DMU

Advanced Journal of Interdisciplinary Studies 9(2025) 2191-2213

AJIDS

Journal homepage: www.ajids.dmu.edu.et

Volume 9(1), June 2025

የተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶ፤ በ7ኛ ክፍል ተተኳሪነት

Amare Teshome Mulatu [1,*], Hailay Tesfay Gebremariam [2]

[1]Department of Ethiopian Language(s) and Literature-Amaharic, College of Social Science and Humanities, University of Gondar, Gondar, Ethiopia.

[2]Department of Ethiopian Languages and Literature-Amharic, College of Social Science and Humanities, Arba Minch University, Arba Minch, Ethiopia. Email: hailay33@gmail.com

[*]Corresponding author email: amare.teshome47@gmail.com or Amare.Teshome@uog.edu.et

አኅጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶን መመርመር ነው። ይህንንም ዋነኛ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን ተከትሏል። ጥናቱ የተካሄደው በፀሃይ ጮራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆን፣ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነትም፣ የጽሑፍ መጠይቅ የተማሪዎቹን የመጻፍ ግለብቃት እምነት ለመለካት፤ እንዲሁም ፈተና የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታን ለመፈተሽ ተግባር ላይ ውለዋል። በሁለቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙትን መረጃዎች በነጠላ ናሙና ቲቴስት፣ በፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ እና በባለብዙ ድህረት የመተንተኛ ዘዴዎች እንዲተነተኑ ተደርጓል። በጥናቱ ውጤት መሰረት የተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነታቸው ($\bar{X}$ = 3.16, <0.05) እና የመጻፍ ችሎታቸው ($\bar{X}$ = 66.54, <0.05) ከተጠባቂ አማካዮቻቸው በተወሰነ ርቀት በልጠዋል፤ እንዲሁም ጉልህ ልዩነት አሳይተዋል። ከውጤቱም በመነሳት የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ በመካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። በሌላ በኩል በመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በመጻፍ ችሎታ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለ (r=0.313, P<0.01) የጥናቱ ውጤት ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በአራቱ የመጻፍ ክሂል አላባውያን (ይዘት (r= 0.395; p< 0.01) ፣ አደረጃጀት (r= 0.186፣ p< 0.01) ፣ ቃላት (r= 0.291፣ p< 0.01) እና የቋንቋ አጠቃቀም (r= 0.226፤ p< 0.01)) መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ ሲታይ፤ በመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በስርዓተ አጻጻፍ መካከል ግን ግንኙነቱ (r= 0.136; p>0.05) ደካማ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። በሌላ መልኩ የመጻፍ ግለብቃት እምነት ከመጻፍ ክሂል አለባውያን መካከል ይዘትን የመተንበይ ሚናው (β=3.42፣ t=3.74፣ P<0.05) የተሻለ እንደሆነ ለመለየት ተችሏል። እንዲሁም የመጻፍ ክሂል አላባውያን በህብር በመጻፍ ግለብቃት እምነት የተተንባይ ሚና እንዳለቻው (R^2= 0.175 ፣ F= 6.271 ፣ P<0.05) የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። በአጠቃላይ ከተገኙ ውጤቶች በመነሳት የተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነታቸው እና የመጻፍ ችሎታቸው በመካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፤ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና አራቱ የመጻፍ ክሂል አላባውያን (ይዘት፣ ቃላት፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና አደረጃጀት) አዎንታዊ መጠነኛ ተዛምዶ አላቸው፤ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና ስርዓተ

አጻጻፍ ተዛምዷቸው ዝቅተኛ ነው፤ እንዲሁም ከመጻፍ ክሂል አላባውያን መካከል የተማሪዎቹ የይዘት ውጤት በመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ የመተንበይ ድርሻው የጎላ ነው:: ወደሚሉ ድምዳሜዎች ሊደረስ ተችሏል:: በመጨረሻም ከጥናቱ ግኝት በመነሳት ለተማሪዎች፣ ለመምህራን ፣ ለስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች እና ለተመራማሪዎች ልዩ ልዩ አስተያየቶች እንዲቀርቡ ተደርጓል::

ቁልፍ ቃላት፤ የመጻፍ ችሎታ ፣ የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ የመጻፍ ክሂል አላባውያን

Abstract

This study investigates the relationship between students' writing self-efficacy and their writing performance. To achieve this main objective, the study followed a correlational research design. The study was conducted among 7th-grade students in Tsehai Chora Primary School. As a data collection instrument, a questionnaire was used to measure the students' writing self-efficacy, and a test was used to investigate the students' writing performance. The data from the two data collection instruments were analysed using a one-sample t-test, Pearson's correlation coefficient, and regression analysis methods. According to the study results, students' writing self -efficacy ($\bar{X} = 3.16$, $p < 0.05$) and writing performance ($\bar{X} = 66.54$, $p < 0.05$) were slightly higher than the expected values, with significant differences observed. These results suggest that the level of students' writing self-efficacy and their achievement in writing skills is moderate. On the other hand, The results of the study also showed that there was a positive correlation between writing self-efficacy and writing performance ($r=0.313$, $P<0.05$). In addition, there was a positive correlation between self-efficacy and four writing skill elements (content ($r = 0.395$; $p < 0.01$), organization ($r = 0.186$; $p < 0.01$), vocabulary ($r = 0.291$; $p < 0.01$), and language use ($r = 0.226$; $p < 0.01$)); however, there was weak relationship ($r= 0.136$; $p>0.05$) between writing self-efficacy and mechanics. On the other hand, writing self-efficacy significantly predicted ($\beta=3.42$, $t=3.74$, $P<0.05$) *the content of students' writing. Furthermore, writing self-efficacy predicted ($R^2= 0.175$ ፣ $F= 6.271$ ፣ $P<0.05$) a significant role in students' overall elements of writing. Based on the overall results, students' writing self-efficacy and writing skill performance are at a medium level; Writing self-efficacy and four writing skill elements (content, vocabulary, language use, and organization) are moderately positively correlated; Writing self-efficacy and mechanics have a weak relationship, and it was also concluded that writing self-efficacy has a predictive role in the elements of content and overall elements of writing performance. Finally, based on the study's findings, various recommendations were made to students, teachers, curriculum developers, and researchers.*

Keywords: Writing Performance, Writing Self-efficacy, Writing Skill Elements

1. የጥናቱ ዳራ

የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ በመጻፍ ትምህርት አውድ ውስጥ ያለውን ሚና

በሚመለከት የተለያዩ ተመራማሪዎችን ቀልብ እየሳበ ይገኛል (Pajares, 2003 ; Schunk, 2003; Zimmerman & Bandura, 1994)። የመጻፍ ክሂል በትምህርት ስርአት ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነና መሰረታዊ የቋንቋ ክሂል ነው። የመጻፍ ችሎታ እየተሻሻለ ሲሄድ ተማሪዎች የተለያዩ ኃላፊነቶችን በመወጣት በቋንቋው የሚኖራቸውን ተጠቃሚነት ያጎላዋል፤ በሚያከናውኗቸው ተግባቦታዊ ሂደቶች ውስጥ የበለጠ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፤ አዳዲስ ሀሳብ የማመንጨትና ሀሳባቸውን በተቃና መልኩ እንዲገልጹ ያስችላቸዋል፤ እንዲሁም ከስነትምህርታዊ ሁነቶች ባሻገር ወደፊት በሚሰማሩባቸው የሙያ መስኮች ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው (Burning & Horn, 2000) ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ Eggleston (2017) እንደሚያስረዱት መጻፍ፣ በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ከሆኑ ክሂሎች አንዱ ሲሆን፣ ከሰዎች ጋር በጽሑፍ ተግባቦት ለመፍጠር ፣ ለማሳመን እና እራስን ለመግለጽ ያስችላል። በሌላ መልኩ Brown (2001) መጻፍ የይዘት፣ የቃላት፣ የአደረጃጀት፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና የስርዓተ አጻጻፍ ድምር ውጤት ነው። እነዚህ የመጻፍ ንዑሳን አላባዎች መጎልበታቸው ተማሪዎች ከክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ ለሚገጥሟቸው ተግባቦታዊ ክስተተቶች እንደግብአት እና እንደችሎታ በመሆን ያገለግላሉ። የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ሊተነብዩ ይችላሉ ተብለው ከሚጠቀሱ ስነልቦናዊ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ደግሞ ግለብቃት እምነት ነው።

ግለብቃት እምነት በ1970 በAlbert Bandura የተዋወቀ ስነልቦናዊ ጽንሰ ሀሳብ ነው። Albert Bandura የማህበረ ግንዛቤያዊ ንድፈ ሀሳብን ባስተዋወቁበት ዘመን ግለብቃት አንዱና ዋነኛ ስነልቦናዊ አተያያቸው ነበር። ምሁሩ፣ በንድፈ ሀሳባቸው ውስጥ ለራስ ያለ እምነት ምን ያህል የሰውን ልጅ ባህሪውን ለመቆጣጠር እንደሚያስችለው እና አንድን ተግባር ለመፈጸም አስተዋጽኦ እንደሚያደርግለት በወቅቱ ለማሳየት ችለዋል። ከ1980-1990 ባሉት አስርት አመታት ውስጥ ደግሞ ከBandura ሀሳብ የተቀዱ ስነልቦናዊ እሳቤዎችን ከመጻፍ ትምህርት ጋር በማቀናጀት የእርስበርስ ግንኙነታቸውን በጥናትና ምርምር ለመፈተሽ ተችሏል። በእነዚህ ዘመናት ውስጥም Flower & Hayes (1981) እና Silvia (1990) የተባሉ ምሁራን አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ይነገራል። ከ1990ዎቹ አጋማሽ በኋላ ደግሞ የመጻፍ ግለብቃት እምነትን ከተለያዩ ስነልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦች ጋር በማያያዝ ጥናትና ምርምር ያደረጉ በርካታ ምሁራን ነበሩ። ከእነዚህም መካከል Pajares (2003) ፣ Schunk (2003) እና Zimmerman and Bandura (1994) የሚጠቀሱ ሲሆን፣ የመጻፍ ግለብቃት እምነትን ከመጻፍ ትምህርት ጭንቀት፣ ከመጻፍ ትምህርት አመለካከት ፣ ከስርዓተ ጾታ ወዘተ ጋር በማያያዝ ልዩ ልዩ ጥናቶችን ማካሄድ ችለዋል ። ከዚህ በተጨማሪ ከ2000 እስከ 2020ዎቹ ባሉት ቀሪ አመታት ደግሞ የመጻፍ ግለብቃት እምነት በመጻፍ ክሂል አላባውያን እና በመጻፍ ችሎታ ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ በተለያዩ የክፍል ደረጃ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ እየተጠና ይገኛል። ለአብነት ያህልም Bassaffar and Alzahrani (2022)፣ Bruning et al. (2013) እና Hetthong and Teo (2013) የተባሉ ምሁራን የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ በመጻፍ ችሎታ እና በመጻፍ ክሂል አላባውያን ላይ ያለውን ሚና

በተለያዩ ጊዜያት ልዩ ልዩ ጥናትና ምርምሮችን አካሂደዋል፡፡ እንዲሁም የመጻፍ ግለብቃትን ከተለያዩ የመማር ብልሃቶች ጋር በማያያዝ የተማሪዎችን በራስ መተማመን ችሎታ በምን ያህል ደረጃ እንደሚያጎለብት ልዩ ልዩ ጥናቶች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡

Bandura (1986) እንደሚገልጹት ግለብቃት እምነት አንድን ተግባር በሚፈለገው መልኩ ከመፈጸም አኳያ የሚሰጥ ግለሰባዊ ውሳኔ ነው፡፡ Pajares (2003) ግለብቃት እምነት ለቋንቋ መማር እና ማስተማር ወሳኝ ስነልቦናዊ ፅሳቤ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የሚያነሱት በራሳቸው የሚተማመኑ ተማሪዎች፣ ለሚማሩት የቋንቋ ትምህርት (ታላሚ ቋንቋ) ተነሳሽነት እንዲኖራቸውና ስኬታማ እንዲሆኑ ስለሚያስችላቸው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Ehrman (1996) እንደሚያስረዱት፣ የግለብቃት ምንነትን ከቋንቋ ትምህርት ጋር በተያያዘ ተማሪዎች በመማር ሂደት ላይ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመፍታት ያላቸው የመቋቋም ችሎታን የሚመለከት ነው፡፡

ከላይ የቀረቡት የግለብቃት እምነት ብያኔዎች በተጨማሪ ከመጻፍ ትምህርት ጋር አያይዘው የግለብቃት ምንነትን በተመለከተ ሀሳባቸውን የሰነዘሩ ምሁራን አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ Hashemenejad et al. (2014) እና Pajares and Vialante (2006) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እንደ Pajares and Vialante (2006) አገላለጽ ግለብቃት እምነት በአጠቃላይ በመጻፍ ችሎታ ተማሪዎች የሚያሳዩት በራስ መተማመን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Hashemenejad et al. (2014) ከመጻፍ ትምህርት ጋር አያይዘው የግለብቃት ምንነትን እንደሚገልጹት፣ ተማሪዎች ከመጻፍ ችሎታቸው ጋር በተያያዘ አለኝ ብለው የሚያምኑት አቅም/ብቃት ነው፡፡ እነዚህም የብቃት/የችሎታ አይነቶች ከመጻፍ ትምህርት ጋር የተያያዙ ንዑሳን ዓላማዎችን ከመጠቀም ጋር የሚያያዙ ሲሆን እነሱም፣ ድርሰት አደራጅቶ መጻፍን፣ ሥርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መጠቀምን፣ የታላሚውን ቋንቋ ፊደል በትክክል መጻፍን ፣ ሰዋስውን ጠብቆ የመጻፍ ተግባር ማከናወንን፣ ወዘተ የሚጠይቁ ናቸው፡፡

ግለብቃት እምነት፣ የተማሪዎችን አእምሯዊ፣ ባህሪያዊ እና ተነሳሽነት መፍጠሪያ ተደርገው ከሚወሰዱ የስነልቦና እሳቤዎች ውስጥ አንዱ ነው (Bandura, 1992)፡፡ በBandura (1997) አተያይ ከፍተኛ የግለብቃት እምነት ባላቸው እና ዝቅተኛ የግለብቃት እምነት ባላቸው መካከል ልዩነት አለ፡፡ ከፍተኛ የግለብቃት እምነት ያላቸው ተማሪዎች በመጻፍ ትምህርት ሂደት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በመፍታት የመጻፍ ችሎታቸውን በሂደት ለማሻሻል ጥረት የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ነገር ግን ዝቅተኛ ግለብቃት እምነት ያላቸው ተማሪዎች በመጻፍ ትምህርት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመቋቋም የሚቸገሩ እና የአቅም ማነስ አለብኝ ብለው ስለሚያምኑ በችሎታቸውም ደካማ የመሆናቸው እድል ሰፊ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ከBandura ጥናት በኋላ የተለያዩ ተመራማሪዎች ግለብቃት እምነትን ከተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር በማያያዝ የተለያዩ ጥናቶችን አድርገዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል Bruning, et al. (2013) የመጻፍ

ግለብቃት እምነትን የተለያዩ ምሁራን (Bandura, 1994; Pajares, 2007; Shell et al., 1995; Zimmerman & Kitsantas, 2007)፣ በየጥናቶቻቸው ያነሷቸውን ነጥቦች መነሻ በማደረግ በሦስት ሞዴሎች ከፍለው አሳይተዋል። የመጀመሪያው ሞዴል የሀሳብ እምነት (Ideation) ነው። በመጻፍ ትምህርት አውድ ውስጥ የተማሪዎች የሀሳብ እምነት ለመጻፍ የሚያግዟቸውን መነሻ ምክንያቶች እንዲያመነጩ እና በድርሰት መጻፍ ሂደት ውስጥ እንዲጠቀሙበት ያስችላቸዋል (De Smedt et al., 2016)። የሀሳብ እምነት ተማሪዎች ስለሚጽፉበት ርዕሰ ጉዳይ በአዕምሯቸው እንዲፈጥሩ፣ እንዲያሰላስሉ እና እንዲያደራጁ እድል ይሰጣቸዋል። እንዲሁም የየራሳቸው ግላዊ አተያይ ላይ መነሻ በማድረግ ለድርሰት የሚጠቅማቸውን ማንኛውንም ጽንሰሀሳብ ከውስጣቸው እንዲያፈልቁ ያስችላቸዋል። ማሰላሰላቸው ደግሞ የመጻፍ ሂደቱን ከመጀመራቸው በፊት የተለያዩ ሀሳቦችን እና ርዕሰ ጉዳዮችን እንዲለዩ ያደርጋቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም የማደራጀት ተግባር መፈጸማቸው ለመጻፍ የሰበሰቧቸውን ሀሳቦች ተጠይቃዊ በሆነ ቅደም ተከተል አቀናብረው ድርሰቶቻቸውን መጻፍ እንዲችሉ አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥርላቸዋል (Bruning et al., 2013)።

ሁለተኛው የመጻፍ ግለብቃት እምነት ሞዴል መዋቅራዊ ስምምነት (conventions) ነው (Bruning et al., 2013)። ሞዴሉ ተማሪዎች የሚጽፉት ጽሑፍ ግልጽ እና ትክክለኛ እንዲሆን ያስችላል። በዚህ ውስጥም ፊደል አጻጻፍ፣ ሰዋስው ፣ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም እና የአጻጻፍ ስርዓት ይካተታሉ። ተማሪዎች ለእነዚህ መሰረታዊ ነጥቦች ትኩረት በሚሰጡበት ጊዜ በመጻፍ ትምህርት ውስጥ የመዋቅራዊ ስምምነታቸው የተሻለ ደረጃ ላይ እንዲገኝ ምክንያት ይሆናል (De Smedt et al., 2023)። ሶስተኛው የመጻፍ ግለብቃት እምነት ሞዴል ራስ መርነት (self-regulation) ነው። ይህም በዋነኝነት ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ሊከወን የሚችል ስነልቦናዊ እሳቤ ነው (Bruning, et al., 2013)። በመሆኑም ራስ መርነት በመጻፍ ሂደት ውስጥ ማለትም፡- አላማ በማውጣት፣ ቢጋር በመንደፍ፣ ረቂቅ በማዘጋጀት፣ የጻፉትን እንደገና በመገምገም እና ዋና ጽሑፉን በመጻፍ ክንውን ውስጥ ተማሪዎች ከግምት ማስገባት ያለባቸውን ስነልቦናዊ እሳቤዎች የሚያካትት ነው (De Smedt et al., 2023)። በዚህ የጥናት ሂደትም Bruning et al. (2013) ስለመጻፍ ግለብቃት እምነት ያነሷቸውን ሞዴሎች መነሻ በማድረግ ከተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ጋር ተዛምዷቸውን ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል።

2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

መጻፍ፣ የአፍልቆት ክሂል እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ሀሳባቸውን ፣ ስሜታቸውን ፣ ፍላጎታቸውን ወዘተ ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ክሂል ነው (Raimes, 1983)። ሆኖም የተለያዩ ጥናቶች (አማረ፣ 2009 እና አማረ 2010) እንደሚያሳዩት የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ በሚፈለገው መልኩ መሻሻልን እያሳየ አይደለም ። ይህን በሚመለከት Alfaki (2015) እንደሚያስረዱት በመጻፍ ትምህርት አውድ ከይዘት፣ ከቃላት፣ ከአረፍተ ነገር አወቃቀር እና ከአደረጃጀት አኳያ ተማሪዎች የተለያዩ ችግሮች ይስተዋልባቸዋል። ለመጻፍ ችሎታቸው አለመሻሻል ደግሞ

በምክንያትነት የሚቀርቡ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ። እነሱም ከስነልቦና ፣ ከግንዛቤ እና ከቋንቋ ችሎታ የሚመነጩ ችግሮች ናቸው (Byrne, 1988)። በመጻፍ ትምህርት ውጤታማ የመማር ማስተማር እንዲፈጠር ስነልቦናዊ ጽንሰሀሳቦችን ከመጻፍ ችሎታ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማጥናት አስፈላጊ ነው (Husna et al., 2021)። ከስነልቦናዊ ጽንሰሀሳቦቹ ውስጥ አንዱ ደግሞ የመጻፍ ግለብቃት ነው።

የተለያዩ ተመራማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶን በሚመለከት ልዩ ልዩ ጥናቶችን አድርገዋል። ከእነዚህም መካከል Hetthong and Teo (2013) የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶን እንግሊዝኛን እንደውጭ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ጥናታቸውን አካሂደዋል። ጥናቱም በ51 ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሲሆን፣ የመጻፍ ግለብቃት እምነታቸውን በጽሁፍ መጠይቅ እንዲሁም የመጻፍ ችሎታቸውን ለመለየት አንቀጽ እንዲጽፉ ተደርጓል። የጥናቱ ውጤትም በመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ በመጻፍ ክሂል አላባውያን እና በአጠቃላይ የመጻፍ ችሎታ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለ አሳይቷል።

Khojasteh et al. (2016) የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶ እንግሊዝኛን እንደውጭ ቋንቋ በሚማሩ የኢራን ተማሪዎች ላይ ጥናት አድርገዋል። ጥናቱም በ28 ወንድ ተማሪዎች እና በ31 ሴት ተማሪዎች ላይ ተካሂዷል። ከጥናቱ የተገኘው ውጤትም በተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በመጻፍ ችሎታ መካከል ምንም አይነት ተዛምዶ እንደሌለ አሳይቷል። ከዚህ በተጨማሪ ከጾታ አንጻር በወንዶች እና በሴት ተማሪዎች መካከል በመጻፍ ችሎታም ሆነ በመጻፍ ግለብቃት እምነት ምንም አይነት ተዛምዶ እንደሌለ የጥናቱ ውጤት ሊያሳይ ችሏል።

Gisella and Roni (2021) በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶን አጥንተዋል። የጥናቱ ውጤትም በመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በመጻፍ ችሎታ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለ አመላክቷል። የተገኘውም የተዛምዶ ውጤት 0.773 ሲሆን፣ ይህም በሁለቱ ተለዋዋጮች መካከል ጠንካራ ተዛምዶ እንዳለ ሊያሳይ ችሏል። ይህም በሌላ አገላለጽ የመጻፍ ግለብቃት እምነት በመጻፍ ችሎታ ላይ የመተንበይ አስተዋጽኦው 59.8% እንደሆነ በጥናቱ ውስጥ ለማሳየት ተችሏል።

Husna et al. (2021) ግለብቃት እምነት በመጻፍ ችሎታ ላይ ያለውን ሚና በሚመለከት በኢንዶኔዥያ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ጥናታቸውን አካሄደዋል። ይህንንም ጥናት ከግብ ለማድረስ ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን የተከተሉ ሲሆን፣ በናሙናነትም 110 ተማሪዎች በጥናቱ ውስጥ ተሳትፈዋል። ጥናቱም በመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በመጻፍ ችሎታ መካከል ጉልህ ተዛምዶ እንደሌለ አሳይቷል። በዚህም የተነሳ የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ በመጻፍ ችሎታ ላይ ያለው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ ነው ወደሚል መደምደሚያ ተደርሷል።

Aldina (2022) የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶን አጥንተዋል። ለዚህም ገላጭ ድርሰት ላይ ያተኮረ ጽሁፍ ለጥናቱ የተጠቀሙ ሲሆን የተማሪዎቹን የመጻፍ

ችሎታ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? የሚለውን እንደተጨማሪ አላማ አካተው ለመፈተሽ ሞክረዋል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት በመካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ የተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና ገላጭ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ መካከል ጉልህ ተዛምዶ እንደሌለ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል።

Bassaffar and Alzahrani (2022) በጅዳ ዩኒቨርሲቲ እንግሊዝኛን እንደውጭ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነታቸው እና የመጻፍ ችሎታቸው ተዛምዶ ምን ያህል እንደሆነ አጥንተዋል። ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና አጠቃላይ የመጻፍ ችሎታ አዎንታዊ መካከለኛ ተዛምዶ እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። ከዚህም በተጨማሪ የመጻፍ አላባ ሆኖ የቀረበው ሰዋስው እና የመጻፍ ግለብቃት እምነት አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳላቸው በጥናቱ ተጠቁሟል። በሌላ በኩል በመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በዝርዝር የመጻፍ ክሂል አላባውያን (ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ቃላት፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና ስርዓተ አጻጻፍ) መካከል ተዛምዶው ዝቅተኛ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

Setyowati et al. (2024) በግል ዩኒቨርሰቲዎች በሚማሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶን እንዲሁም ደረጃን የፈተሸ ጥናት ነው። በዚህም ጥናት 55 ተማሪዎች የተሳተፉ ሲሆን፣ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንዳሳየው የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት በመካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ እንዲሁም በመጻፍ ግለብቃት እምነታቸው እና በመጻፍ ችሎታቸው መካከል ምንም አይነት ተዛምዶ እንደሌለ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። ከጥናቱ ከተገኘው ውጤት በመነሳት ተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነታቸውን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ተከታታይ የመጻፍ ተግባራትን እና ምጋቤ ምላሾችን መምህራኑ በመስጠት ለመጻፍ ችሎታ ያለውን አስተዋጽኦ ማጎልበት እንደሚቻል በአስተያየት መልክ መጠቆም ችለዋል።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች፣ የተለያዩ ውጤቶችን አሳይተዋል። በአንድ በኩል፣ የመጻፍ ግለብቃት እና የመጻፍ ችሎታ ጉልህ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳላቸው ያሳዩ ጥናቶች አሉ (Basaffar and Alzahrani, 2022; Gisella and Roni, 2021; Hetthong & Teo, 2013)። በሌላ በኩል ደግሞ፣ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ጉልህ ተዛምዶ እንደሌላቸው የተለያዩ ጥናቶች (Aldina, 2022; Husna et al., 2021; Basfar and Alzahrani, 2022; Khojasteh et al., 2016; Setyowati et al., 2024) አመላክተዋል።

በሌላ መልኩ የመጻፍ ግለብቃት እምነት በመጻፍ አላባውያን እና በአጠቃላይ የመጻፍ ችሎታ ላይ የመተንበይ ሚናቸውን በተመለከተ ውስን ጥናቶች ቢሆኑም፣ የተለያዩ የጥናት ውጤቶችን አሳይተዋል። በBasaffar and Alzahrani (2022) ጥናት የመጻፍ ግለብቃት፣ የመጻፍ ክሂል አላባውያን በሆኑት ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ቃላት፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና ስርዓተ አጻጻፍ የመተንበይ ሚና የላቸውም የሚል የጥናት ውጤት ተገኝቷል። በHetthong and Teo (2013) ጥናት የመጻፍ ግለብቃት እምነት የመጻፍ ክሂል አላባውያንን እና

አጠቃላይ የመጻፍ ችሎታን የመተንበይ ሚና እንዳላቸው ተጠቅሷል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች መረዳት የሚቻለው የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ የተዛምዶ ደረጃ በልዩ ልዩ ጥናቶች የተገኘው ውጤት በአንድ በኩል ጉልህ ተዛምዶ አለ፤ በሌላ በኩል ጉልህ ተዛምዶ የለም የሚሉ መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛዎቹ ቀደምት ጥናቶች የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና አጠቃላይ የመጻፍ ችሎታን ተዛምዶ የፈተሹ ናቸው፡፡ ሆኖም የመጻፍ ግለብቃት እምነትን ከመጻፍ ችሎታ ባሻገር ከመጻፍ ክሂል አላባውያን ጋር ተዛምዷቸውን የፈተሹ ጥናቶች ውስን ናቸው፡፡ የፈተሹትም ቢሆኑ የደረሱባቸው የጥናት ግኝቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመጻፍ ግለብቃት እምነት በእያንዳንዱ የመጻፍ ክሂል አላባ ላይ የመተንበይ ድርሻው ምን ያህል እንደሆነ በቀደምት ጥናቶች በዝርዝር ሊጠና አልቻለም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተጠኑት ሁለት ጥናቶችም ግኝቶቻቸው የተለያዩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመጨረሻም ሁሉም ጥናቶች የወሰዷቸው የናሙና መጠኖች ውስን መሆናቸው እንዲሁም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ውስጥ የተጠኑ ጥናቶች መገኘት አለመቻላቸው በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናቱ እንዲያተኩር ምክንያት ሆኗል፡፡

በመሆኑም የቀደምት ጥናቶች ግኝት የተለያየ መሆኑ፣ ዝርዝር የመጻፍ ክሂል አላባውያን ከተዛምዶ አንጻር በበቂ ያልተፈተሹ መሆናቸው፣ የተለዋዋጮቹን የትንበያ ድርሻ ከመለየት አንጻር የምርምር ክፍተቶች መታየታቸው፤ ሁሉም ጥናቶች በናሙናነት የወሰዷቸው ተማሪዎች ውስን መሆናቸው፤ እንዲሁም ሁሉም ጥናቶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ አውድ መጠናታቸው ለዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህ ጥናትም ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ሊሰጥ ችሏል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ፡-

1. የተማሪዎች የመፃፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ምን ያህል ነው?
2. የተማሪዎች የመፃፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶ ምን ያህል ነው?
3. የተማሪዎች የመፃፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ክሂል አለባውያን ተዛምዶ ምን ያህል ነው?
4. የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ በመጻፍ ክሂል አላባውያን ላይ የመተንበይ ድርሻው ምን ያህል ነው?

3. የጥናቱ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የተማሪዎችን የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶ መመርመር ነው፡፡ ይህንን ዋነኛ ዓላማ ለማሳካት ተዛምዷዊ የምርምር ንድፍ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በፀሃይ ጮራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፣ ትምህርት ቤቱ በአመቺ ንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡ በየትኛውም ቦታ ማንኛውንም ጥናት ማካሄድ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ምርምር በአስተዳደራዊ ድጋፍ ካልተደገፈ ጠቃሚ መረጃዎችን መሰብሰብ የማይቻል በመሆኑ ትምህርት ቤቱ በአመቺ የንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡

የክፍል ደረጃው የተመረጠው በአላማ ተኮር ንሞና ስልት ነው፡፡ ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት ከ5 እስከ 8 ባሉ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ አማርኛን እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ከ7ኛ ክፍል በስተቀር ሌሎቹ አንድ-አንድ ምድብ ብቻ በመሆናቸውና የተማሪ ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ የጥናቱን አስተማማኝነት ዝቅ ሊያደርጉት ይችላሉ በሚል ስጋት 7ኛ ክፍል በአላማ ተኮር ንሞና ዘዴ እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ከመካከለኛ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ 7ኛ ክፍል ተማሪዎች በ3 ምድብ ተከፍለው የሚማሩ በመሆናቸው የዚህ ጥናት ተተኳሪ ሊሆኑ ችለዋል፡፡

7ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎችን ለመምረጥ ጠቅላይ ንሞና ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በክፍል ደረጃው ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የቆዩ ሦስት ምድቦች (162 ተማሪዎች) የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል፡፡ ሆኖም በምርምሩ ውስጥ ከተካተቱት 162 ተማሪዎች መካከል 4 ተማሪዎች ሁለቱንም መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ላይ ያልሞሉ በመሆናቸው፣ 2 ተማሪዎች ደግሞ የጽሑፍ መጠይቁን በትክክል ባለመሙላታቸው እንዲሁም 2 ተማሪዎች አንዱን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ላይ ብቻ መረጃ በመስጠታቸው ከጥናቱ ውጪ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ከ162 ተማሪዎች ውስጥ 154 ተማሪዎች መረጃውን በትክክል በመሙላታቸው የተነሳ ተመራማሪዎቹ የጥናቱ ናሙና በማድረግ በትንታኔ ሂደት ውስጥ ሊጠቀሙበት ችለዋል፡፡

በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የጽሑፍ መጠይቅ እና ፈተና አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ የተማሪዎቹን የመጻፍ ግለብቃት እምነት ለመለካት ተግባር ላይ ውሏል፡፡ መጠይቁም በLikert Scale የአጠያየቅ ስልት የተዘጋጀ ነው፡፡ የLikert Scale የአጠያየቅ ስልት ስነልቦናዊ እሳቤዎችን ለመለካት በቋንቋ ምርምር ውስጥ ታዋቂነት እና ተቀባይነትን እንዳገኘ በተለያዩ ምሁራን ዘንድ ይነገራል፡፡ Brown and Rodgers (2002) እንደሚገልጹት በLikert Scale የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ የመማር ስልትን፣ ተነሳሽነትን ፣ የመማር ብልሃቶችን፣ ወዘተ ለመለካት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የLikert Scale የአጠያየቅ ስልትን (በጣም እስማማለሁ(5)፣ እስማማለሁ(4)፣ መወሰን ያስቸግረኛል(3)፣ አልስማማም(2)፣ እና በጣም አልስማማም(1)) የሚሉትን የመወሰኛ ደረጃዎችን በመጠቀም የተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት ለመለካት ጥረት ተደርጓል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ 16 ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን፣ የተወሰደው ከ Bruning et al. (2013) መጠይቅ ላይ ነው፡፡ በውስጡ የመጻፍ ግለብቃት ሞዴሎች የሆኑ ሦስት ስነልቦናዊ እሳቤዎችን አካቷል፡፡ እነሱም የሀሳብ እምነት፣ መዋቅራዊ ስምምነት እና ራስ መርነት ላይ ያተኮሩ ሦስት አይነት መለኪያዎች ተካተዋል፡፡ የጽሑፍ መጠይቁ ከተዘጋጀ በኋላ በሁለት የፍልስፍና የዶክትሬት ድግሪ አማርኛ ቋንቋ ማስተማር መምህራን ከተገመገመ በኋላ፣ ድል በትግል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች አስተማማኝነቱ እንዲለካ ተደርጓል፡፡ አስተማማኝነቱም በክሮንባኽ አልፋ የተፈተሸ ሲሆን፣ የክሮንባኽ አልፋ ውጤት 0.732 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ከ0.7

በላይ በመሆኑ አስተማማኝ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ፈተና ነው፡፡ ዓላማው የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ለመፈተሽ ነው፡፡ ፈተናውን ለማዘጋጀት፣ የክፍል ደረጃ መርሃ ትምህርቱን ማየት አስፈላጊ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሰፊ ትኩረት የተሰጠው አስረጂ ድርሰት በመሆኑ የተነሳ፣ ተማሪዎቹ አስረጂ ድርሰት መጻፍ እንዳለባቸው ትምህርት ተገኝቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎቹ የሚጽፉበት ርዕስ ጉዳዮች ከእለት ተዕለት ህይወታቸው ጋር የተቆራኘ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም በክፍል ደረጃው አቻ ለሆኑ ሌሎች ተማሪዎች አራት አማራጭ ርእሶች ቀርቦላቸው በአንደኝነት ድርሰት ለመጻፍ የመረጡት ርዕስ፣ በፈተና መልክ ተዘጋጅቶ በዋናው ጥናት ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

Weigle (2002) እንደሚገልጹት የመጻፍ ክሂልን በተንታኝ የማረሚያ ዘዴ ከቀረቡ የመስፈርት አይነቶች መካከል በJacobs et al. (1981) የቀረበው የማረሚያ መስፈርት በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለና የተሻለ ሊባል እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ በማረሚያ ሞዴሉ መሰረት የተማሪዎችን ድርሰት ለማረም፡- ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ቃላት፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና ሥርዓተ አጻጻፍ የተለያየ የውጤት ደረጃ ወጥቶላቸው እና በእያንዳንዱ አላባ ስር ከእጅግ በጣም ጥሩ እስከ በጣም ዝቅተኛ ድረስ በቅደም ተከተል መለኪያ ወጥቶላቸው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ ይህን ሞዴል ከሚደግፉ ምሁራን መካከልም Heaton (1990) ይጠቀሳሉ፡፡ በአጠቃላይ በማረሚያ ሞዴሉ መሰረት፣ ይዘት (30%) አደረጃጀት (20%) ቃላት (20%) የቋንቋ አጠቃቀም (25%) እና ሥርዓተ አጻጻፍ (5%) ውጤቶችን ይዘዋል፡፡ በዚህም የማረሚያ ሞዴል መነሻነት የፈተናው ውጤት በሶስት ኮፒ ከተዘጋጀ በኋላ፣ ሦስት አራሚዎች በማረም ሂደቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በሌላ መልኩ የፈተናውን አስተማማኝነት ለመለካት ድል በትግል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን መጠቀም ተችሏል፡፡ የአራሚዎቹም የስምምነት ደረጃ በክሮንባኽ አልፋ እንዲሳላ ተደርጓል፡፡ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በድርሰት ፈተናው ላይ አራሚዎቹ ያላቸው የስምምነት ደረጃ (α= 0.84) ከፍተኛ እንደሆነ ለመገንዘብ ተገኝቷል፡፡

ፓራሜትራዊ የስታትስቲክስ አይነቶችን ለመጠቀም መሟላት የሚገባቸው እሙኖች አሉ፡፡ በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው የመተንተኛ ዘዴዎች ነጠላ ናሙና ቲቴስት፣ ፒርሰን እና ባለብዙ ድህረት በመሆናቸው እሙኖቹን ማሟላት-አለማሟላታቸውን ተፈትሸዋል፡፡ መልቲኮሊኒያሪቲ የመጀመሪያው እሙን ሲሆን፣ ከዚህ አንጻር የተመዘገበው የVIF ውጤት፣ ይዘት 1.5፣ አደረጃጀት 1.99፣ ቃላት 2.06፣ የቋንቋ አጠቃቀም 1.28 እንዲሁም ስርዓተ አጻጻፍ 1.26 ሆነው ተመዝግበዋል፡፡ የተገኙት ውጤቶችም ከ10 ያልበለጡ በመሆናቸው የተነሳ በተለዋዋጮቹ መካከል ተጽዕኖ የሚፈጥር ተዛምዶ እንደሌለ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የመረጃ ስርጭት ወጥነት ሌላኛው እሙን ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በጥናቱ የተሳተፉት ከ50 በላይ በመሆናቸው የኮልሞጎሮቭ - ሲሚርኖቭ ስሌት ውጤት እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በአምስቱ የመጻፍ ክሂል አላባውያን ፣በመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በመጻፍ

ችሎታ የተመዘገቡ የመረጃ ስርጭት የጉልህነት ውጤቶች ከ0.05 በላይ በመሆናቸው እሙኑን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ አፈንጋጭነት ሌላኛው እሙን ነው፡፡ ከዚህ አኳያም በመጻፍ ችሎታ ፣ በመጻፍ ክሂል አላባውያን እና በመጻፍ ግለብቃት እምነት ውጤታቸው ውስጥ አፈንጋጭ ነጥቦች (outliers) አለመኖራቸው በቦክስ ፕሎት (Boxplot) ግራፍ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ቀጥተኛነት ሌላኛው እሙን ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በተለዋዋጮቹ መካከል ያለው ግንኙነት ኩርባዊ ግንኙነት (curvilinear relationship) ሳይሆን፣ ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳላቸው በብትን ግራፍ ውስጥ ለማየት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ከየእሙኖቹ የተገኙ ውጤቶች መረጃዎቹ ፓራሜትራዊ በሆኑት የመተንተኛ ዘዴዎች መተንተን እንደሚችሉ አመላክተዋል፡፡

በመሆኑም የተማሪዎቹን የመጻፍ ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመለየት ገላጭ ስታትስቲክስ፣ የመጻፍ ግለብቃት እምነታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመለየት ደግሞ ነጠላ ናሙና ቲቴስት በመረጃ መተንተኛ ዘዴነት አገልግሏል፡፡ በሌላ በኩል የተማሪዎቹን የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶን ለመፈተሽ ፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ተግባር ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ የመጻፍ ችሎታን እና የመጻፍ ክሂል አላባውያንን የመተንበይ ድርሻውን ለመለየት ባለብዙ ድህረት የመተንተኛ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

4. የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት የመጀመሪያ መሰረታዊ ጥያቄ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ምን ያህል ነው? የሚል ነበር፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት በገላጭ ስታትስቲክስ የመተንተኛ ዘዴ ሲተነተን የተገኘው ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

4.1 የመጻፍ ክሂል አላባውያን እና የመጻፍ ችሎታ በነጠላ ናሙና ቲቴስት

ሰንጠረዥ 1. የመጻፍ ክሂል አላባውያን እና የመጻፍ ችሎታ በነጠላ ናሙና ቲቴስት

	ናሙና	ተጠባቂ አማካይ	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የቲ ዋጋ	ጉልህነት (Sig)
ይዘት	154	15	19.43	3.54	15.51	0.000
አደረጃጀት	154	10	14.36	2.78	19.44	0.000
ቃላት	154	10	14.29	2.37	22.43	0.000
የቋንቋ አጠቃቀም	154	12.5	15.42	3.28	11.03	0.000
ሥርዓተ አጻጻፍ	154	2.5	3.04	0.90	4.13	0.001
አጠቃላይ የመጻፍ ችሎታ	154	50	66.54	9.69	16.14	0.000

ሰንጠረዥ 1 የተማሪዎቹን የመጻፍ ክሂል ችሎታን ከመጻፍ ክሂል አላባውያን አንጻር ያገኙትን አማካይ ውጤት የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም ይዘት $\bar{X}$ = 19.43; SD = 3.44፣ አደረጃጀት $\bar{X}$ = 14.36; SD = 2.78፣ ቃላት $\bar{X}$ = 14.29; SD = 2.37፣ የቋንቋ

አጠቃቀም $\bar{X}$ = 15.42; SD = 3.28፣ ሥርዓተ አጻጻፍ $\bar{X}$ = 3.04; SD = 0.90 እንዲሁም የመጻፍ ችሎታ $\bar{X}$ = 66.54; SD = 9.69 ውጤቶች ተመዝገበዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በእያንዳንዱ የመጻፍ ክሂል አላባውያን እና በአጠቃላይ የመጻፍ ችሎታ የተመዘገቡት የቲ ዋጋዎች ከዜሮ የራቁ መሆናቸው ከመነጻጸሪያ ዋጋቸው ልዩነት እንደፈጠሩ ያመለክታል፡፡ በዚህም ምክንያት በእያንዳንዱ መለኪያ የተገኙ የጉልህነት ውጤቶች ከ0.05 በታች ሆነው ተመዝግበዋል፡፡ ከተገኙት ውጤቶች በመነሳት የተማሪዎቹ የመጻፍ ክሂል አላባውያን እና የመጻፍ ችሎታ ውጤት አጥጋቢ ባይሆንም በመካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

4.2 የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት በነጠላ ናሙና ቲቴስት

የተማሪዎቹን የመጻፍ ግለብቃት እምነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መፈተሽ ሌላኛው የዚህ ጥናት ትኩረት ነበር፡፡ ከዚህ አንጻር የተገኘው የጥናት ውጤት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 2 የሚያመለክተው በመጻፍ ግለብቃት እምነት ከሚካተቱ ሦስት ሞዴሎች አንጻር የተገኘውን ውጤት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከሞዴሎቹ ውስጥ አንዱ የሆነው የሀሳብ እምነት ሲሆን፣ ከዚህ አኳያ የተገኘው የጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው በተራ ቁጥር 2፣3፣4 እና 5 የቀረቡ መለኪያዎች ከመፈተሻ ዋጋቸው (3) በላይ ሆነው በመገኘታቸው እና ጉልህ ልዩነት በማሳየታቸው የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት አንጻራዊ በሆነ መልኩ የተሻለ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ በተመሳሳይ በተራ ቁጥር 8፣ 9 እና 10 የመጻፍ ግለብቃትን ከመዋቅራዊ ስምምነት አንጻር የተማሪዎቹ ምላሽ ሲታይ ከመፈተሻ ዋጋው (3) በላይ አማካይ ውጤቶች እንደተመዘገቡና ጉልህ ልዩነት እንደተገኘ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከራስ መርነት አንጻር የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እንደሚያሳየው በተራ ቁጥር 11፣13፣14 እና 15 የተገኙ ውጤቶች የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት ከማነጻጸሪያ አማካዩ በላይ በመሆናቸው እና ጉልህ ልዩነት በማሳየታቸው አንጻራዊ የሆነ የተሻለ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

በሌላ በኩል ተራ ቁጥር 7 (መዋቅራዊ ስምምነት) እና 13 (ራስ መርነት) ከመፈተሻ ዋጋው በታች በመሆናቸውና እና ጉልህ ልዩነት በማሳየታቸው ከእነዚህ ከተጠቀሱት መለኪያዎች አንጻር የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት ዝቅተኛ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ሊያሳይ ችሏል፡፡ በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት ከሀሳብ እምነት፣ ከመዋቅራዊ ስምምነት እና ከራስ መርነት አኳያ አብዛኞቹ መለኪያዎች ከመፈተሻ ዋጋቸው በተወሰነ ደረጃ ከፍ በማለታቸው እና አጠቃላዩ አማካይ 3.16 ሆኖ በመመዝገቡ የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት አንጻራዊ በሆነ መልኩ የተሻለ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

4.3 የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶ ትንተና

የዚህ ጥናት ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ የተማሪዎች የመፃፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶ ምን ያህል ነው? የሚል ነበር። ይህን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የጥናቱ ውጤት ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 2. የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት በነጠላ ናሙና ቲቴስት የመተንተኛ ዘዴ

የመጻፍ ግለብቃት እምነት ሞዴሎች	ተ.ቁ	መለኪያዎች	የመፈተሻ ዋጋ = 3			
			አማካይ	መደበኛ ልይይት	የቲ ዋጋ	ጉልህነት (Sig.)
የሀሳብ እምነት	1	ጽሑፌን ለመጻፍ ብዙ ሀሳቦችን ማሰብ እችላለሁ።	3.05	1.34	0.423	0.673
	2	ሐሳቦቼን በጽሑፍ ማስፈር እችላለሁ።	3.26	1.30	2.48	0.014
	3	ሐሳቤን ለመግለጽ ብዙ ቃላትን ማሰብ እችላለሁ።	3.34	1.23	3.41	0.001
	4	ብዙ ከውስጤ የሚመነጩ ሀሳቦችን ማሰብ እችላለሁ።	3.38	1.22	3.87	0.000
	5	ሐሳቦቼን በጽሑፌ ውስጥ የት ቦታ ላይ ማስቀመጥ እንዳለብኝ በትክክል አውቃለሁ።	3.21	1.24	2.14	0.034
መዋቅራዊ ስምምነት	6	በጽሑፌ ውስጥ የምጠቀማቸውን ቃላት በትክክል መጻፍ እችላለሁ።	3.10	1.25	0.97	0.334
	7	የተሟሉ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ እችላለሁ።	2.64	1.18	0.27	0.042
	8	ለጻፍኳቸው አረፍተ ነገሮች በትክክል ስርአተ ነጥቦችን መጠቀም እችላለሁ።	3.32	1.24	3.20	0.002
	9	ሰዋስዋዊ ስርዓታቸውን የጠበቁ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ እችላለሁ።	3.24	1.27	2.34	0.021
	10	አንቀጾቼን በትክክለኛው ቦታ መጀመር እችላለሁ።	3.20	1.20	2.08	0.039
ራስ መርነት	11	ቢያንስ ለአንድ ሰዓት ያህል በጽሑፌ ላይ ማተኮር እችላለሁ።	3.22	1.20	2.29	0.023
	12	በምጽፍበት ጊዜ ትኩረት እንዳልሰጥ የሚያደርጉ ነገሮችን ማስወገድ እችላለሁ።	3.12	1.26	1.15	0.252
	13	የቤት ስራዎችን ለመስራት በፍጥነት እጀምራለሁ።	2.75	1.24	2.55	0.012
	14	በምጽፍበት ጊዜ ድብርት ወይም ድካም ሲሰማኝ መቆጣጠር እችላለሁ።	3.25	1.16	2.63	0.009

	15	ከመጻፊ በፊት የምጽፍበትን አላማ አስባለሁ።	3.40	1.12	4.38	0.000
	16	አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳን መጻፌን እቀጥላለሁ።	3.09	1.21	0.94	0.351
አጠቃላይ አማካይ		**3.16**				

ሠንጠረዥ 3. የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶ ውጤት ትንተና በፒርሰን የተዛምዶ መተንተኛ ዘዴ

	የመጻፍ ችሎታ	**የመጻፍ ግለብቃት እምነት**
የመጻፍ ችሎታ	1	0.323
ጉልህነት (Sig.)		0.000
ናሙና	154	154
የመጻፍ ችሎታ	0.313	1
ጉልህነት (Sig.)	0.000	
ናሙና	154	154

Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed)

ሰንጠረዥ 3 የሚያሳየው የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶን ነው። የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ አዎንታዊ ተዛምዶ አላቸው ($r=0.313$, $P<0.01$)። ይህም ውጤት በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል መጠነኛ አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን ያሳያል። ተሰልቶ ከተገኘው ውጤት የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነት እየጨመረ በሄደ ቁጥር የመጻፍ ችሎታቸውም መጠነኛ በሆነ መልኩ እየጨመረ እንደሚሄድ መረዳት ይቻላል።

4.4 የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ክሂል አላባውያን ተዛምዶ

የዚህ ጥናት ሶስተኛው መሰረታዊ ጥያቄ የተማሪዎች የመፃፍ ግለብቃት እምነት እና ዝርዝር የመጻፍ ክሂል አለባውያን ተዛምዶ ምን ያህል ነው? የሚል ነበር። ይህን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 4 በመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በአምስቱ የመጻፍ ክሂል አለባውያን መካከል ያለውን ግንኙነት ያሳያል። በዚህ መሠረት የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በአራቱ የመጻፍ ክሂል አላባውያን (ይዘት ($r= 0.395$; $p< 0.01$) ፣ አደረጃጀት ($r= 0.186$፣ $p< 0.01$) ፣ ቃላት ($r= 0.291$፣ $p< 0.01$) እና የቋንቋ አጠቃቀም ($r= 0.226$፤ $p< 0.01$)) መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለ ያሳያል ።

ሠንጠረዥ 4. **የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ክሂል አላባውያን ተዛምዶ፤ በፒርሰን የተዛምዶ መተንተኛ ዘዴ**

	1	2	3	4	5	6
1.ይዘት የፒርሰን ተዛምዶ	1					
ጉልህነት (Sig.)						
ናሙና	154					
2.አደረጃጀት የፒርሰን ተዛምዶ	0.467	1				
ጉልህነት (Sig.)	0.000					
ናሙና	154	154				
3. ቃላት የፒርሰን ተዛምዶ	0.525	0.649	1			
ጉልህነት (Sig.)	0.000	0.000				
ናሙና	154	154	154			
4.የቋንቋ አጠቃቀም የፒርሰን ተዛምዶ	0.370	0.446	0.485	1		
ጉልህነት (Sig.)	0.000	0.000	0.000			
ናሙና	154	154	154	154		
5.ሥርዓተ አጻጻፍ የፒርሰን ተዛምዶ	0.356	0.416	0.303	0.241	1	
ጉልህነት (Sig.)	0.000	0.000	0.000	0.003		
ናሙና	154	154	154	154	154	
6. የመጻፍ ግለብቃት እምነት የፒርሰን ተዛምዶ	**0.395***	**0.186***	**0.291***	**0.226***	**0.136**	1
ጉልህነት (Sig.)	**0.000**	**0.001**	**0.000**	**0.005**	**0.092**	
ናሙና	**154**	**154**	**154**	**154**	**154**	154

**ጉልህ ተዛምዶ በ0.01 ደረጃ (2-ጫፍ)

ነገር ግን በመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በስርዓተ አጻጻፍ መካከል ግንኙነቱ ደካማ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ በአጠቃላይ ከተገኙት ውጤቶች መረዳት የሚቻለው የመጻፍ ግለብቃት እምነት እየጨመረ በሄደ ቁጥር የይዘት፣ የአደረጃጀት ፣ የቃላት እና የቋንቋ አጠቃቀም ውጤቶች በመጠነኛ ደረጃ እየጨመሩ እንደሚመጡ ሲያሳይ፤ በመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በስርዓተ አጻጻፍ መካከል ግን ግንኙነቱ (r= 0.136; p>0.05) ደካማ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ሊያሳይ ችሏል፡፡

4.5 የመጻፍ ግለብቃት እምነት በመጻፍ ክሂል አላባውያን ላይ የመተንበይ ድርሻ

አራተኛው የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄ የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ በመጻፍ ክሂል አላባውያን ላይ የመተንበይ ድርሻው ምን ያህል ነው? የሚል ነበር፡፡ ይህንንም መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ በባለብዙ ድህረት የመተንተኛ ዘዴ ሲሰላ የተገኘው ውጤት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 5. የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ በመጻፍ ክሂል አላባውያን ላይ የመተንበይ ድርሻ በባለብዙ ድህረት መተንተኛ ዘዴ

የመጻፍ ክሂል አላባውያን	የተጋርቶ መጠን (R^2)	ድህረታዊ መጣኝ (β)	መደበኛ ስህተት (Std. Error)	መደበኛ ድኅረታዊ መጣኝ (Beta)	የቲ ዋጋ (t)	ጉልህነት (Sig.)
ይዘት	0.175	0.067	0.018	3.42	3.74	0.000
አደረጃጀት		0.025	0.026	0.09	0.94	0.348
ቃላት		0.043	0.031	0.15	0.14	0.165
የቋንቋ አጠቃቀም		0.015	0.019	0.07	0.80	0.425
ሥርዓተ አጻጻፍ		0.007	0.065	0.01	0.10	0.918

ሰንጠረዥ 5፣ የመጻፍ ግለብቃት እምነት ፣ የመጻፍ ክሂል አላባውያን የመተንበይ ድርሻውን ያሳያል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው የተንባይ ሚና ያለው የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ ከመጻፍ ክሂል አላባውያን ውስጥ ይዘትን (β=3.42፣ t=3.74፣ P<0.05) የተሻለ የመተንበይ ድርሻ እንዳለው ከተመዘገቡት ስሌቶች መረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም ሌሎቹ የመጻፍ ክሂል አላባውያን በተናጠል የተተንባይነት ሚና እንደሌላቸው በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል የመጻፍ ክሂል አላባውያኑ በቅንጅት በመጻፍ ግለብቃት እምነት የመተንበይ ሚና እንዳላቸው (R^2= 0.175 ፣ F= 6.271 ፣ P<0.05) የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በአጠቃላይ የተገኘው የጥናት ውጤት ይዘት፣ ከሌሎቹ አላባዎች ሲነጻጸር የተሻለ የተተንባይነት ድርሻ እንዳለው ሲያሳይ፤ የመጻፍ ክሂል አላባውያኑ በህብር የተተንባይነት ሚናቸው ደግሞ 17.5 % መሆኑን በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ቀሪው 82.5% ከመጻፍ ግለብቃት እምነት ውጪ ባሉ ሌሎች ነጻ ተለዋዋጮች ሊገለጹ የሚችሉ መሆናቸውን ጥናቱ በተጨማሪነት አመላክቷል፡፡

5. የውጤት ማብራሪያ

በዚህ ጥናት የመጀመሪያው መሰረታዊ ጥያቄ የነበረው የተማሪዎች የመፃፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ምን ያህል ነው? የሚል ነበር፡፡ ይህንን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ በገላጭ እና በነጠላ ናሙና ቲቴስት መረጃዎች እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የተማሪዎቹ የመጻፍ ችሎታ ደረጃ ማለትም ይዘት $\bar{X}$ = 19.43; SD = 3.44፣ አደረጃጀት $\bar{X}$ = 14.36; SD = 2.78፣ ቃላት $\bar{X}$ = 14.29; SD = 2.37፣ የቋንቋ አጠቃቀም $\bar{X}$ = 15.42; SD = 3.28፣ ሥርዓተ አጻጻፍ $\bar{X}$ = 3.77; SD = 0.90 እንዲሁም አጠቃላይ የመጻፍ ችሎታ $\bar{X}$ = 67.26; SD = 9.69 ውጤቶች ተመዝገበዋል፡፡ እነዚህም በመጻፍ ክሂል አላባውያን የተመዘገቡት አማካዮች ከሚጠበቁት አማካዮች ጋር ተቀራራቢ በመሆናቸው የተነሳ የተማሪዎቹ የመጻፍ ችሎታ

በመካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። ይህም የተገኘው ውጤት ቀደም ሲል ከተጠኑ ቀደምት ጥናቶች መካከል ከBassaffar and Alzahrani (2022) ጥናት ጋር የተደጋገፈ ውጤት ተገኝቷል።

በዚህ ጥናት ሁለተኛ መሰረታዊ ጥያቄ የነበረው የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የአጠቃላይ የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶ ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ ነው። ይህንን ዋነኛ ዓላማ ለመመለስ ፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት በመረጃ መተንተኛ ዘዴነት ጥቅም ላይ ውሏል። ከጥናቱ የተገኘው ውጤትም እንደሚያሳየው የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ አዎንታዊ ተዛምዶ ያላቸው (r=0.313, P<0.01) መሆኑን ነው። ይህም የተገኘው የተዛምዶ ውጤት መጠነኛ ሊባል የሚችል ነው። ቀደም ሲል ከተጠኑ ጥናቶችም (Bassaffar & Alzahrani, 2022; Gisella and Roni 2021; Hetthong & Teo, 2013) የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ አዎንታዊ ተዛምዶ አላቸው ከሚሉት የጥናት ውጤት ጋር ተደጋግፏል። ሆኖም ግን የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶ ዝቅተኛ ነው ከሚለው (Aldina, 2022; Husna et al., 2021; Khojasteh et al., 2016; Setyowati et al., 2024) የጥናት ውጤት ጋር የተቃረነ ሆኖ ተገኝቷል።

የተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ክሂል አላባውያን ተዛምዶ ምን ያህል ነው? የሚለውን መፈተሽ ሌላኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ ነበር። ይህንንም ዓላማ ለመመለስ በፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ እንዲሰላ ተድርጓል። የተገኘው ውጤትም እንደሚያሳየው የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በአራቱ የመጻፍ ክሂል አላባውያን (ይዘት (r= 0.395; p< 0.05)፣ አደረጃጀት (r= 0.186፣ p< 0.01)፣ ቃላት (r= 0.291፣ p< 0.01) እና የቋንቋ አጠቃቀም (r= 0.226፤ p< 0.01)) መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ ሲያሳይ፤ ነገር ግን በመጻፍ ግለብቃት እምነት በስርዓተ አጻጻፍ መካከል ግን ግንኙነቱ ደካማ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ይህም የጥናት ውጤት ቀደም ሲል ከተጠኑ ጥናቶች መካከል Hetthong and Teo (2013) የመጻፍ ግለብቃት እምነት፡- ከይዘት፣ ከአደረጃጀት፣ ከቃላት እና ከቋንቋ አጠቃቀም ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳላቸው ከጠቆሙት የጥናት ውጤት ጋር የተደጋገፈ ሆኖ ተገኝቷል። ሆኖም Basaffar and Alzahrani (2022) የመጻፍ ግለብቃት እምነት ከይዘት፣ ከአደረጃጀት እና ከቋንቋ አጠቃቀም እና ተዛምዶው ዝቅተኛ ነው ካሉት የጥናት ውጤት ጋር የተቃረነ ሲሆን፣ ከስርዓተ አጻጻፍ ጋር ተዛምዶ ዝቅተኛ ነው ካሉት የጥናት ውጤት ጋር ደግሞ የተደጋገፈ ሆኖ ተገኝቷል።

የመጨረሻው የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄ የነበረው የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ በመጻፍ ክሂል አላባውያን ላይ የመተንበይ ድርሻው ምን ያህል ነው? የሚል ነበር። ይህንንም ለመለየት ባለብዙ ድህረት በመተንተኛ ዘዴነት ጥቅም ላይ ውሏል። በጥናቱ ትንተና ሂደትም የመጻፍ ግለብቃት እምነት ተንባይ እንዲሁም ይዘት፣ አደረጃጀት ፣ቃላት ፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና ስርዓተ አጻጻፍ የተተንባይ ሚና እንዲኖራቸው ተደርጎ ተሰልቷል። በዚህም መሰረት ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የመጻፍ ግለብቃት እምነት ከመጻፍ ክሂል አለባውያን መካከል ይዘትን

የመተንበይ ሚናው (β=3.42፣ t=3.74፣ P<0.05) የተሻለ እንደሆነ ለመለየት ተችሏል። እንዲሁም የመጻፍ ክሂል አላባውያን በህብር በመጻፍ ግለብቃት እምነት የተተንባይ ሚና እንዳለቸው (R^2= 0.175 ፣ F= 6.271 ፣ P<0.05) የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። ይህም ውጤት ከቀደምት ጥናቶች መካከል Hetthong and Teo (2013) የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ የመጻፍ ችሎታን የመተንበይ ሚና እንዳለው ከጠቀሱት የጥናት ውጤት እንዲሁም Bandura (1986, 1997) የመጻፍ ግለብቃት እምነት በቋንቋ ችሎታ ላይ ተንባይ ተላውጦ ነው ካሉት ሀሳብ ጋር የተደጋገፈ ሆኗል። በሌላ በኩል Basaffar and Alzahrani (2022) ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ቃላት እና የቋንቋ አጠቃቀም የተተንባይ ድርሻ እንደሌላቸው ከጠቆሙት የጥናት ውጤት ጋር የተቃረነ ሆኖ ተገኝቷል።

6. ማጠቃለያና መደምደሚያ

ይህ ተዛምዷዊ ጥናት በዋነኝነት ትኩረት ያደረገው የተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶን በመፈተሽ ላይ ነው። ጥናቱ የተካሄደው በ2016ዓ.ም በ7ኛ ክፍል ደረጃ ሲማሩ በነበሩ 154 ተማሪዎች ላይ ነው። መረጃዎችን ለመሰብሰብ የጽሑፍ መጠይቅ እና ፈተና አገልግለዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎችም በነጠላ ናሙና ቲቴስት፣ በፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ እና በባለብዙ ድህረት የመተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል። የውጤት ትንተናውም የተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታ በመካከለኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አሳይቷል። በሌላ በኩል በተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና በይዘት ፣ በአደረጃጀት፣ በቃላት ፣ በቋንቋ አጠቃቀም እና በመጻፍ ችሎታ መካከል መካከለኛ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። ሆኖም የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የአጻጻፍ ሥርዓት ተዛምዷቸው ደካማ መሆኑን በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል። በሌላ መልኩ ከመጻፍ ክሂል አላባውያን ውስጥ ይዘት፣ በመጻፍ ግለብቃት እምነት የተሻለ የተተንባይነት ሚና እንዳለው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ከዚህ በተጨማሪ የመጻፍ ክሂል አላባውያኑ በቅንጅት በመጻፍ ግለብቃት እምነት የተተንባይነት ድርሻ እንዳላቸው በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል። ከእነዚህም ውጤቶች በመነሳት የሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ ተደርሷል። በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች፡-

- የመጻፍ ግለብቃት እምነታቸው እና የመጻፍ ችሎታቸው በመካከለኛ ደረጃ ላይ ይገኛል።
- በመፃፍ ግለብቃት እምነታቸው እና በመጻፍ ችሎታቸው መካከል መጠነኛ አዎንታዊ ተዛምዶ አለ።
- የመፃፍ ግለብቃት እምነታቸው እና በመጻፍ ክሂል አላባውያን ውጤቶቻቸው (ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ቃላት እና የቋንቋ አጠቃቀም) መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ አለ።
- በመፃፍ ግለብቃት እምነታቸው እና በስርዓተ አጻጻፍ ውጤታቸው መካከል ተዛምዶው ዝቅተኛ ነው።
- ከመጻፍ ክሂል አላባውያን መካከል የይዘት ውጤታቸው በመጻፍ ግለብቃት እምነት፣ የመተንበይ ድርሻው የጎላ ነው።

7. አስተያየት

ጥናቱ ይዞት ከተነሳው አላማ እና ከተገኙ ውጤቶች በመነሳት የሚከተሉት

አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡ የመጀመሪያው፡- የጥናቱ ውጤት፣ የተማሪዎች የመጻፍ ግለብቃት እምነት እና የመጻፍ ችሎታቸው አዎንታዊ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያመለክተው የተማሪዎቹ የመጻፍ ግለብቃት እምነታቸው በጨመረ ቁጥር የመጻፍ ችሎታቸውም እየተሻሻለ እንደሚመጣ ነው፡፡ በመሆኑም፡-
መምህራን የመጻፍ ትምህርትን ሲያስተምሩ ተማሪዎቹ ራሳቸውን እንዲመዝኑ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ሂደትም በመጻፍ ክሂል ውስጥ ስላሉ አላባዎች በቂ ግንዛቤ በመፍጠር ለእያንዳንዱ የመጻፍ ክሂል አላባ ትኩረት እንዲሰጡ በማድረግ በመጨረሻም ከአላባዎቹ አንጻር ራሳቸውን እንዲገመግሙ እድል በመስጠት የመጻፍ ግለብቃት እምነታቸውን በሂደት እንዲጎለብት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንጻር መምህራን ያላከናወኗቸው ተግባራት ካሉ በመጻፍ ትምህርት ሂደት ውስጥ ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

የመጻፍ ክሂልን ተማሪዎቹ የበለጠ እንዲያሻሽሉ ለማድረግ በመጽሃፉ የሚቀርቡ ተግባራት ተግባቦታዊ አውድ የተመሰረቱ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መማሪያ መጽሃፉ ተማሪዎቹ ልዩ ልዩ የመጻፍ ብልሃቶችን እንዲጠቀሙ እድል የሚሰጡ እንዲሁም ከእለት ተእለት ህይወታቸው ጋር የተዛመዱ መሆናቸው የመጻፍ ክሂልን በሚፈለገው መልኩ እንዲለማመዱት እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ በመጻፍ ትምህርት አውድ በራስ መተማመናቸው እንዲጨምርና የሚሰጣቸውን ማንኛውንም የመጻፍ ተግባር በሚፈለገው መልኩ እንዲሰሩ እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች ትኩረት ያልተሰጣቸው ጉዳዮችን በመለየት ለቀጣይ ማስተካከያ የሚሹ ጉዳዮችን ከግንዛቤ አስገብተው መጠቀም ቢችሉ ጥሩ የመጻፍ ትምህርት አውድ መፍጠር እንደሚቻል አጥኚዎቹ ያምናሉ፡፡

በሌላ በኩል ተመራማሪዎች፣ ከተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ጋር ተያያዥነት ሊኖራቸው የሚችሉ ሌሎች ስነልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦች ላይ ተመስርተው ተዛምዷዊ ጥናት ማካሄድ ቢችሉ አዎንታዊ የመጻፍ ትምህርት አውድ ለመፍጠር በሚደረግ ሂደት ውስጥ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አጥኚዎቹ ያምናሉ፡፡

ምስጋና

መረጃ መሰብሰብ እንድንችል አስተዳደራዊ ድጋፍ ላደረጉልን የፀሃይ ጮራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ከልብ ለማመስገን እንወዳለን፡፡ እንዲሁም የጥናቱን አላማ ለማሳካት በሚል እሳቤ መረጃዎችን በተገቢው መልኩ በመሙላት ለተባበሩን የፀሃይ ጮራ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች እና የቁሳቁስ አቅርቦት በማሟላት ምርምሩ እንዲካሄድ ላደረገልን የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

ዋቢዎች

አማረ ሰውነት፡፡(2009)፡፡ “ችግርመር የመማር ዘዴ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂልና የመፃፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት የሚኖረው ሚና፤ አፍ መፍቻ ቋንቋና ያታ ተኮር ጥናት፤ በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አማርኛ ትምህርት ክፍል አንደኛ አመት ተማሪዎች ተተኳሪነት”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የዶክትሬት ድግሪ ማሟያ ጥናት፡፡

አማረ ተሾመ ፡፡(2010)፡፡ “ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው ተጽዕኖ (በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት)”፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የዶክትሬት ድግሪ ማሟያ ጥናት፡፡

Aldina, V. (2022). The correlation between students' self-efficacy in writing descriptive text and their writing performance. *Research on English Language Teaching in Indonesia* 10 (02), 75-82. https://ejournal.unesa.ac.id/index.php/retain/article/view/46085

Alfaki, I. M. (2015). University students' English writing problems: Diagnosis and remedy. *International journal of English language teaching*, *3*(3), 40-52.

Bandura, A. (1986). *Social foundations of thought and action:A social cognitive view* . Prentice Hall.

Bandura, A. (1992). Social cognitive theory of social referencing. In S. Feinman (Ed.), Social referencing and the social construction of reality in infancy (pp. 175-208). New York: Plenum.

Bandura, A. (1994). Self-Efficacy. In V. S. Ramachandran (Ed.), Encyclopedia of Human Behavior (Vol. 4, pp. 71-81). New York: Academic Press. (Reprinted in H. Friedman (Ed.) (1998). Encyclopedia of Mental Health. San Diego: Academic Press).Oxford University Press.

Bandura, A. (1997). Self-Efficacy: The Exercise of Control. W.H. Freeman and Company, New York.

Basaffar, F. M., & Alzahrani, W. A. (2022). The Relationship between Self-Efficacy and Writing Achievement among English as a Foreign Language Learners at the University of Jeddah. *Journal of Arts, Literature, Humanities and social sciences* (84), 182-198. https://doi.org/10.33193/JALHSS.84.2022.737

Brown, D. (2001). *Teaching by Principles: An Interactive Approach to language Pedagogy* (2nd ed.) New York, Addison Wesley Longman.

Brown, J. D., & Rodgers, T. S. (2002). *Doing second language rese arch*. Oxford, Oxford University Press.

Bruning, R., Dempsey, M., Kauffman, D. F., McKim, C., & Zumbrunn, S. (2013). Examining dimensions of self-efficacy for writing. *Journal of Educational Psychology, 105*(1), 25–38. https://doi.org/10.1037/a0029692

Bruning, R., & Horn, C. (2000). Developing motivation to write. *Educational psychologist*, 35(1), 25-37. https://doi.org/10.1207/S15326985EP3501_4

Byrne, D. (1988). *Teaching Writing Skills*. Longman: Longman Group UK Lmited.

De Smedt, F., Landrieu, Y., De Wever, B., & Van Keer, H. (2016). The role of writing motives in the interplay between implicit theories, achievement goals, self-efficacy, and writing performance. *Frontiers in Psychology*, *14*, (1149923), 1-11. https://doi.org/10.3389/fpsyg.2023.1149923

Eggleston, B. (2017). "Relationship between Writing Self efficacy and Writing Fluency in a performance Feedback Intervention" (Unpublished Master's thesis) Syracuse University, Syracuse, N.Y.

Ehrman, M.E. (1996). *Understanding Second Language Learning Difficulties*. London, Sage Publications, Inc. https://doi.org/10.4135/9781452243436

Flower, L. and Hayes J. (1981). A Cognitive Process Theory of Writing. *College Composition and Communication*. 32 (4), 365-387. https://doi.org/10.2307/356600

Gisella, I. Roni, R. Mulyadi (2021). The Correlation between Self-Efficacy and Writing Achievement of Undergraduate Students. *Journal PendidiKan Tambusai*, 5(1), 2230-2236. https://doi.org/10.31004/jptam.v5i2.1654

Hashemenejad, F. Zoghi, M. and Amini, D. (2014). The Relationship between Self-efficacy and Writing Performance across Genders. *Theory and Practice in Language Studies*, 4 (5). 1045-1052. 1045-1052. 10.4304/tpls.4.5.1045-1052

Heaton, J. B. (1990). *Writing English language tests*. London, Longman Ltd.

Hetthong, R., and Teo, A. (2013). Does writing self-efficacy correlate with and predict writing performance? *International Journal of Applied Linguistics & English Literature,* 2(1), 157-167. https://doi.org/10.7575/ijalel.v.2n.1

Husna, A., Ningrum, A. S. B., and Rohmah, G. N. (2021). The Role of Self-Efficacy in Writing Achievement of Indonesian Senior High School Students. *Edulingua: Jurnal Linguistiks Terapan dan Pendidikan Bahasa Inggris*, *8*(1), 51-58. https://doi.org/10.34001/edulingua.v8i1.1602

Jacobs, H.L., Zinkgraf, S.A., Wormuth, D. R., Hartfiel, V.F., & Hughey, J. B. (1981). Testing ESL composition: A practical approach. Rowley, MA: Newbury House.

Khojaste, L. Shokrpour, N. and Afrasiabi, M. (2016). The relationship between writing self-efficacy and writing performance of Iranian EFL students. *International Journal of Applied Linguistics and English*

Literature, 5 (4), 29-37. https://doi.org/10.7575/aiac.ijalel.v.5n.4p.29

Pajares, F. (2003). Self-efficacy beliefs, motivation, and achievement in writing: A review of the literature. *Reading &Writing Quarterly,* 19(2), 139-158. https://doi.org/10.1080/10573560308222

Pajares, F. (2007). Empirical Properties of a Scale to Assess Writing Self-Efficacy in School Contexts. *Measurement and Evaluation in Counseling and Development, 39*(4), 239–249. https://doi.org/10.1080/07481756.2007.11909801

Pajares, F., and Valiante, G. (2006). Self-Efficacy Beliefs and Motivation in Writing Development. In C. MacArthur, S. Graham, & J. Fitzgerald (Eds.), *Handbook of Writing Research* (pp. 158-170). New York, NY: Guilford Press.

Raimes, A. (1983) *Techniques in Teaching Writing*. Oxford: Oxford University Press.

Schunk, D. H. (2003). Self-efficacy for reading and writing: Influence of modeling, goal setting, and self-evaluation. *Reading & Writing Quarterly: Overcoming Learning Difficulties, 19*(2), 159–172. https://doi.org/10.1080/10573560308219

Setyowati, L., Sukmawan, S., Karmina, S., & Mabaroh, B. (2024). The Correlation between Students' Writing Self-Efficacy and Essay Writing Performance. *Journal of Languages and Language Teaching*, *12*(1), 72-87. https://doi.org/10.33394/jollt.v12i1.9140

Shell, D. F., Colvin, C., & Bruning, R. H. (1995). Self-efficacy, attribution, and outcome expectancy mechanisms in reading and writing achievement: Grade-level and achievement-level differences. *Journal of Educational Psychology, 87*(3), 386–398. https://doi.org/10.1037/0022-0663.87.3.386

Silva, T. (1990). Second language composition instruction: Development, issues, and directions. In ESL B. Barbara Kroll, (ed.), *Second language writing: Research insights for the classroom* (pp. 11-23). Cambridge: University Press.

Weigle, S. C. (2002). *Assessing Writing*. Cambridge: Cambridge University Press.

Zimmerman, B. J., & Bandura, A. (1994). Impact of self-regulatory influences on writing course attainment. *American Educational Research Journal, 31*(4), 845–862. https://doi.org/10.2307/1163397

Zimmerman, B., & Kitsantas, A. (2007). Reliability and validity of self-

efficacy for learning form (SELF) scores of college students. *Zeitschrift für Psychologie/Journal of Psychology*, *215*(3), 157-163. DOI:10.1027/0044-3409.215.3.157